# ኢማም ሁሴን መስጂድ

## መርካቶ - አደሬ ሠፈርን ያቀናው ቀደምት መስጂድ!

**የተመሠረተበት ዘመን:-** መጋቢት 9/1949

**የሚገኝበት አካባቢ:-** መሀል መርካቶ፣ በምዕራብ ሆቴልና በበርበሬ በረንዳ መሀከል፣ በተለምዶ «አደሬ ሠፈር» ተብሎ በሚጠራው መንደር፣ አስፋልት መንገድ ዳር ይገኛል::

**መግቢያ:-**

ከአዲስ አበባ መስጂዶች ውስጥ 99.9% ቦታቸውን ያገኙት በግዢ አልያም በወቅፍ (ግለሰቦች ከንብረታቸው በስጦታ መልክ) ነው:: ከመንግስት ቦታ ጠይቆ በነፃ የተገኘ ካለ 0.1% ከሆነ ነው:: ይህም አንድ የሚገርም ነገር ነው:: ይህንን ያነሳሁት ያለምክንያት አይደለም:: ኢማም ሁሴን መስጂድም የተገኘው በወቅፍ መሆኑን ለማስታወስ ነው::

እንዴት በወቅፍ እንደተገኘ ከመመልከታችን በፊት ጥቂት ስለ አደሬ ሠፈር ላውጋ:: የሀረሪ ብሄረሰብ ተወላጆች ወደ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ በአንድ አካባቢ ተሰባስበው ይኖሩ ነበር:: በተለይም ከጣሊያን ወረራ በኋላ ሙስሊሞች እርስት የመያዝ ዕድላቸው እየሰፋ በመሄዱ ወደ 7 ሰዎች አካባቢ በጋራ ሆነው በአሁኑ አደሬ ሠፈር አካባቢ ይሠፍራሉ (1930ዎቹ):: ይህ የሆነው መርካቶ የገበያ ማዕከል የተቋቋመው በዛ አካባቢ ስለሆነ ነው:: በሂደትም አያሌ የሀ ረሪ ተወላጆች ወደዚህ ሠፈር በመምጣታቸውና በመኖራቸው «የአደሬ ሠፈር» ተብሎ ሊጠራ ችሏል:: በኋላ ላይ ደግሞ በኳስ ሜዳ አካባቢ፣ በመካኒሳ አካባቢዎች የሀረሪዎች. . . መሰሉ የጋራ መንደር ምስረታ ተካሂደዋል:: ቢሆንም ግን ዋናውና ቀደምቱ አሁን የምናወራው አደሬ ሠፈር ነው:: በዚህም ምክንያት በአደሬ ሠፈር ዘመድ አዝማድ የሌለው የሀረሪ ተወላጅ የለም::

**ከምስረታ በፊት:-** ታሪኩን ልንዘክርለት በመንደርደር ላይ ያለነው መስጂድ ከመመስረቱ በፊት የጀመዓ ሶላት የሚሰገደው በሐጂ አህመድ ዩኑስ ሸሪፍ ቤት ነበር:: እኚህ ሰው ኢማም ሀሰን መስጂድን የወቀፉት የሐጂ አብዱላሂ ዩኑስ ሸሪፍ ታናሽ ወንድም ናቸው:: ቤታቸውም እዛው አደሬ ሠፈር፣ አባድር መድረሣ አጠገብ ነው:: ቤቱ አሁንም ድረስ ያለ በመሆኑ እኔም





ለመመልከት ችያለሁኝ:: በዚህ ቤት አንድ ክፍል የተጀመረው ጀመዓ በሂደት እንዴት ፍሬ እንዳፈራ ቀጥለን እንመለከታለን::

**አመሰራረት:-** በመጋቢት 9/1949 ሐጂ አብዱላሂ ዩኑስ ሸሪፍ የተባሉ ነጋዴ በአጎታቸው በሐጂ አቡበከር ሸሪፍ ቤት ተቀምጠው ሳለ «ይህንን ቦታዬና ቤቴን ለመስጂድ ልወቅፈው አስቤአለሁኝ» ሲሉ ያወራሉ:: አጎታቸውም ይህንን እንደሰሙ «እንግዲያውስ ንያ ካለህ ዛሬውኑ አድርገውና ይፃፍ» ይሏቸዋል (ኸይር ሥራን ማሳደር አይወደድምና)::

ሌላውም በዙሪያቸው የነበረው ሁሉ «አዎን! ዛሬ ይሁን ዛሬ. . .!» በማለት ድጋፋቸውን ይሰጡዋቸዋል:: ሐጂ አብዱላሂም በውስጣቸው ጨርሰው ነበርና «ይሁን:: አሁን !» አሉ:: የደስታ «አላሁ አክበር!» በቤቱ ተሰማ:: በዚህች ቅጽበት በአካባቢው አንድ መስጂድ ተፈጠረ ማለት ነው:: ወዲያው ወረቀት መጣ፣ ተፃፈ፣ ተፈረመ::

በዛን ጊዜ በእጅ የተፃፈው የወቅፍ ስጦታ ስምምነትም እስከ ዛሬ በጥንቃቄ ተቀምጦ እነሆ ለታሪክ ቀርቧል:: በዚህ አጋጣሚም ቤተሰባቸውንና የመስጂዱ ኮሚቴዎችን ከልብ ማመስገን ይኖርብናል:: ምክንያቱም የዛሬ 53 ዓመት የተ ፃፈውን ዶክመንት ማስቀመጥ በመቻላቸው ነው:: መረጃ የማስቀመጥ ልምድ የሌለን ሁሉ ከዚህ ልንማር ይገባናል::

ሐጂ አብዱላሂ ዩኑስ ሸሪፍ በአካባቢው ቤቶችን በመግዛት ያከራዩ ነበር:: ወቅፍ ያደረጉት ቤትም ራሳቸው የሚኖሩበት ቤት ሳይሆን በዚሁ ዓላማ የገዙት ቤት ነው:: የርሳቸው ቤት ወቅፍ ካደረጉት ቦታ አጠገብ ነበር:: አሁንም በወራሾቻ ቸው እጅ ይገኛል:: ሐጂ አብዱላሂ ቤቱንና መሬቱን ወቅፍ አድርገው ብቻ አልተቀመጡም:: በቦታው የነበረውን ቤት አፍርሰው በራሳቸው ወጪ መስጂዱን ገነቡ:: የገነቡት መስጂድም እስካሁን በማገልገል ላይ ይገኛል:: መስጂዱ እስካሁን አንድም የቅርጽም ሆነ የስፋት ለውጥ አልተካሄደበትም:: መስጂዱን ሲገነቡ «አንድ ታሪካዊ መረጃም በአንቦሃ ጠርሙስ ውስጥ አድርገው በመሰረቱ ውስጥ ቀብረዋል ሲሉ ሐጂ ካሚል ሸሪፍ ያስረዳሉ:: ይህም መስጂዱ መቼ ወቅፍ እንደተደረገ፣ በማን እንደተደረገ፣ የመሬቱ ስፋት. . .የሚገልፅ መረጃ ነው ተብሏል:: ይህንንም ያደረጉት «በእጅ የተቀመጠው ሰነድ ቢጠፋ እንኳ ለወደፊቱ መስጂዱ ፈርሶ መታደሱ ስለማይቀር የዛኔ መ ረጃው እንዲገኝ በማለት ነው» ሲሉ ሐጂ ሸሪፍ ይገልፃሉ:: እንግዲህ በርሳቸው

የተገነባው መስጂድ በዘመናዊ አሻሽሎ ለመስራት አሁን እንቅስቃሴው ስላለ መስጂዱ ሲፈርስ ይህንን ሰነድ የማግኘቱና የማውጣቱ ጉዳይ ከወዲሁ ሊታሰብበት ይገባል እንላለን:: እንደተባለው ካለም ጠርሙሱ ሳይሰባበር፣ ከቦታው ሳይወጣም. . .ባለበት ሁኔታ ፎቶ-ግራፍ ማንሳት፣ ጋዜጠኞችን ጠርቶ ማሳየትና ሌሎችንም ጋብዞ ማስጎብኘት ለታሪኩ ውበትና ድምቀት ይሰጠዋል:: አስተማሪም ይሆናል::

<u>የቤተሰቦቻቸው ድጋፍ:-</u> ሐጂ አብዱላሂ ዩኑስ ሸሪፍ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ላበረከቱት ላቅ ያለ አስተዋጽኦ የቤተሰቦቻቸው ድጋፍ ከፍ ያለ ነበር:: በተለይም ባለቤታቸው ሐጂየት ነፊሣ ሙሐመድ ሙዲር ላቅ ያለውን የማበረታቻ ድጋፍ እንደቸሩዋቸው ሐጂ ካሚል ያብራራሉ:: ሐጂየት ነፊሣ አባታቸው ሙፍቲ ሙሐመድ ሙዲር በሀረር የታወቁና ላቅ ያለ አክብሮት ያላቸው «ሙፍቲህ» መሆናቸውም ጨምረው ገልፀዋል::

እንደዚሁም አጎቶቻቸው ሐጂ አቡበከር ሸሪፍ፣ ሐጂ ኢብራሂም ሸሪፍ፣ ወንድማቸው ሐጂ አህመድ ዩኑስ ሸሪፍ የቅርብ ድጋፍ፣ ምክርና ማበረታቻ በመስጠት እስከ መጨረሻ ከጎናቸው ሆነዋል::

<u>የመስጂዱ አስተዳደር (ናዚር):-</u> የመስጂዱን ቦታ በወቅፍ ሰጥተው፣ መስጂዱን አስገንብተው ታላቅ ውለታ የሰሩት ሐጂ አብዱላሂ ስለ አስተዳደሩም በወቅፍ ስምምነቱ ላይ ያስቀመጡት ነገር አለ:: ይህም በሕይወት እስካሉ እርሳቸው ሙሉ ወጪውን እየቻሉ ሊያስተዳድሩት፣ ከርሳቸው በኋላ ደግሞ ታላቁ ልጃቸው ተውፊቅ አብዱላሂ እንዲያስተዳድረው፣ ከዛ ቀጥሎ ለማስተዳደር ብቃት ያለው ከርሳቸው ዘር የሆነ፣ ብቃት ያለው ባይገኝ ደግሞ ከአባታቸው ወገኖች ከሀረሪዎች የሆነ፣ ከዚህም ባይገኝ ከሀረርጌ ተወላጅ ሙስሊሞች ተመርጦ ሊሾም፣ ይህም ባይሳካ ከማንኛውም ወገን የሆነ ሙስሊም ተመርጦ ናዚር (አስተዳደር) እንዲሆን የሚል ነው::

በዚህም መሰረት መስጂዱ ሐጂ አብዱላሂ በሕይወት እስካሉ ድረስ በርሳቸው መሪነት ሲመራ ነበር:: ወደ አኼራ የሄዱትም በ1968 አካባቢ ነው:: በመቀጠልም ልጃቸው ሐጂ ተውፊቅ አብዱላሂ ተረክበው አስተዳድረውታል:: በኋላ ግን ሐጂ ተውፊቅ ሠፈራቸው እዛ ስላልነበር አስተዳደርነቱን ለአጎታቸው ለሐጂ አህመድ ዩኑስ ሸሪፍ አስተላለፉት:: ሐጂ አህመድም እስከ 1983 ድረስ ሲያስተዳድሩት ነበር::

ከ1983-1990 ደግሞ አቶ ነስረዲን አህመድ ዩኑስ ሸሪፍ ይዘውት ነበር:: ከ1990-





1999 ሐጂ አብዱልቃድር ርዝቂ፣ አቶ አብደላህ ኢብራሂም፣ አቶ አወል ሳቢር፣ ሐጂ አብዱረህማን መሐመድ፣ አቶ አማን አህመድ፣ ሸኽ ኸድር ሐጂ አደምና አቶ ነስረዲን አህመድ በኮሚቴነት መርተውታል::

<u>የይዞታ ስፋት:-</u> ወደ 389 ካ.ሜ የሚሆን ይዞታ አለው:: ከመጀመሪያ ይዞታው ትንሽ በ1967ቱ አዋጅ የተወረሱበት ቤቶች አሉ:: በመጀመሪያ ሐጂ አብዱላሂ ያስረከቡት ቦታ ሁለት ጊዜ የተገዛና የሰፋ ነበር:: 245.52 ካ.ሜና ቀሪው 143.48 በተለያየ ሰውና ጊዜ ገዝተው በመቀላቀል ነበር በድምሩ 389 ካ.ሜ ቦታ ስፋት ያለው መስጂድ የወቀፋት:: ከመስጂዱ የተቀነሰው ክፍል እንዲመለስ በተለያየ ጊዜ ከመንግስት ጋር የተፃፃፈ ሲሆን አሁንም ሂደቱ እንደቀጠለ ነው:: ይዞታው ካርታ ያለው ነው::

<u>የሰጋጁ ብዛት:-</u> በመስጂዱ ውስጥ ከነግቢው ወደ 200 ሰዎች ይሰግዳሉ:: ነገር ግን የሰጋጁ ቁጥር ከ1000 በላይ ሲሆን በዙሁር፣ በአስርና በመግሪብ ሰዓታት አስፋልቱ ሁሉ ተነጥፎ ይሰገዳል:: ከመስጂዱ 100 ሜትር ወደታች ድረስ አስፋልቱ ተነጥፎ ይሰገድበታል:: ይህንንም ችግር በዘላቂነት ለመፍታት አዲሱ የመስጂዱ አስተዳደር እቅድ አውጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል::

<u>*መድረሣ:-*</u> በመስጂዱ ውስጥ መድረሣ የለም:: ነገር ግን በ1952 የተቋቋመው የአባድር መድረሳ በአካባቢው የሚገኝና ከመስጂዱ ጋር ተዛማጅና ተወራራሽ ሆኖ ይገለፃል::

<u>ኢማሞች:-</u>

1. ራሳቸው ሐጂ አብዱላሂ
2. ሸኽ ያሲን (አል ስልጤ)
3. ሸኽ ኸድር

<u>*ሙአዚኖች:-*</u>

ሸኽ አብዶሽ ሸሪፍ (በረመዳን ወር ውስጥ በየቤቱ እየዞሩ «ተስኸሩ» በማለት ይቀሰቅሱ ነበር ይባላል)::

<u>የመስጂዱ ኮሚቴዎች</u>

1. ሐጂ ኢልያስ አህመድ ሸሪፍ. . . . . . . . . . . . . . .ሰብሳቢ
2. ሐጂ አህመድ ሁሴን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .ም/ሰብሳቢ

3. አቶ ኢብራሂም ሰኢድ. . . . . . . . . . . . . . . . . .ፀሃፊ
4. አቶ ሚፍታህ ኢብራሂም. . . . . . . . . . . . . . . . . .ገ/ያዥ
5. አቶ አብድሽኩር አብደላህ. . . . . . . . . . . . . . . . . .ሂ/ሹም
6. አቶ አህመድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .አባል
7. አቶ ነጂብ አደም. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ..አባል
8. አቶ ፈቱ ሻፊ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . የጉባኤ ሊቀ መንበር

<u>መስጂዱን የማሳደግ እቅድ፡-</u> ከላይ የተጠቀሰው የመስጂዱ ኮሚቴ የተቋቋመው በ1999 መጨረሻ ነሐሴ ወር ነው፡፡ በአዲስ መልኩ የመቋቋመው ለሁለት ዋና ዓላማዎች ነው፡፡ መስጂዱ ቋሚ የገቢ ምንጭ ስለሌለው በሂደት ወደ ሚስኪንነት በመሄዱ ይህንን በዘላቂነት ማስወገድ አንደኛው ዓላማ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከሠጋጁ መሀከል በመስጂዱ ውስጥ ቦታ አግኝቶ የሚሰግደው 1/4ኛው ብቻ ነው፡፡ ቀሪው 3/4ኛው የሚሰግደው ውጭ በአስፋልት ላይ አንጥፎ ነው፡፡ በመሆኑም ዘመናዊ መስጂድ በመገንባት ይህንን ችግር መቅረፍ ለመቻል ነው፡፡

ሁለቱም ዓላማዎች በመሳካት ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ አዲሱ የመስጂዱ ኮሚቴ ጠንክሮ በመንቀሳቀሱ በአሁኑ ወቅት የመስጂዱ ጊዜያዊ ወጪዎች በመሟላት ላይ ናቸው፡፡ ለወደፊቱ ደግሞ G+3 ዘመናዊ መስጂድ ለመገንባት አርክቴክቸራል ዲዛይኑ ወጥቶ በመስጂዱ በር ላይ ተሰቅሏል፡፡ ለዚህም ግንባታ መጀመር አንዳንድ የቦታው ጉዳዮችና የፕላን ፈቃዶች በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ ይህ ሲጨረስ በቀጥታ ወደ ግንባታው እንደሚገባ የኮሚቴው ሰብሳቢ ሐጂ ኤልያስ አስረድተዋል፡፡ ለመስጂዱ ግንባታ ከዚህ በፊት ቃል የገባ ሰው እንዳለ ጠቅሰው ሌሎችም አህለል ኸይራት ጉዳዩን በጉጉት የሚጠብቁት በመሆኑ በግንባታው ወጪ ምንም የሚያስጋቸው እንደሌለ አስረድተዋል፡፡ የሚገነባው መስጂድም G+3 የሆነ በጣም ዘመናዊ መስጂድ እንደሚሆን አስታውሰዋል፡፡ ይህም ከ5 ሚሊዮን የማያንስ ወጪ እንደሚፈጅ ተገምቷል፡፡

<u>የመረጃ ምንጭ</u>

1. ሐጂ ካሚል
2. ሐጂ ኤልያስ አህመድ

<u>የስልክ አድራሻ፡-</u>

0911-54 74 74